# ምሰሶው ለጥ አለ!

  

## ባለማተቡ ሊቀ-ሊቃውንት

ምርጋቱ ፍርሶ ግርግዳውም ነቅዞ፣
ጉንጉኑ በስብሶ ማገሩም ተፍቶ፣
ወጋግራው ተሰብሮ አእዋፉም ተጭሮ፣
ምሰሶው ለጥ አለ ጥቁሩ አሞራ ከብዶ፡፡

የሊቃውንቱ አባት የቅኔው ማህደር፣
ደራሲ ተርጓሚ የግእዙም ዘማር፣
ለም-ጭንቅላት ይዞ ሄደ ወደ ጠፈር፣
ከመሬትም ገባ ደግሞ ሊመራመር፡፡

መንፈስህን ገላህን ሁሉን አውርሰሃት፣
የእምነት ካባ አልብሰህ ሙሽራ አድርግሃት፣
ሊቃውንት እንድትወልድ በመስቀለ ባርከሃት፣
ጸበል ፃድቅ ቀምሰን እኛም አድገንባት፣
መቼም ያች ቦታ የግፍ ማህጸን ናት፣
ቤትህ ነፈገችህ ተስካርና ፍታት፣
እነ ሆድ አምላኩ ዘለው ሰፈረውባት፡፡

እኒያ እምታውቃቸው ጦምህን ያሳደሩህ፣
አንተን ዝቅ ያረጉ መስሏቸው የጎዱህ፣
በምድር በሰማይም ከፍ ከፍ አረጉህ፡፡

ቆፍጣናው በሐሪህ ግራ ያጋባቸው፣
እሳቱ መንፈስህ ከሩቅ የፈጃቸው፣
በቀል መበቅያ ሙት ገላህ ሆናቸው፡፡

የመሰረትከውን ገዳሙን ዘጉብህ፣
ማእረግና ክብርን አልፈህም ሊነፍጉህ፣
ከፍነው ገንዘው በቁም ስለፈቱህ፡፡

የእውነት ያለህ እያልክ እድሜ ልክ ስለጮህ፣
ምግብ ዉኃ ነስተው በምድር ስለቀጡህ፣
ጥርጥር የለኝም ወደላይ እንዳረግህ፣
ምድረ- ፈሪሳዊን ረግጠህ ተራምደህ፣
ሙሴን ኤልያስን እንደተገናኘህ፣
ከጌታ በስተቀኝ በክብር ቁጭ እንዳልክ፡፡

ቅኔውና ዜማው ገልጦ እማይጭርስህ፣
ጸናጽል በፉጨት ጠርቶ እማይሰለችህ፣
ከበሮ አወድሶ አንስቶ እማይጠግብህ፣
ሊቀ-ሊቃውንቱ ያገር በረከት ነህ፣
ዘላለም ይነበብ አያሌው ታምርህ፣
ኢትዮጵያም ትነሳ እንድታስታውስህ፡፡

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ነሐሴ ፲፱፻፺፱ ዓ. ም.